# ኢትዮጵያ እጆቿን ወደእግዚያብሔር ትዘረጋለች፣

ከማተቤ መለሰ ተሰማ
ሐምሌ2001

የሁላችንም፡ ሰሞነኛ መናጋገሬያ አጀንዳ ሆኖ የቆየው፡ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክሥ፡ ተዋህዶ ሐይማኖት ሲኖዶሥ፡ አባላትና በፓትርያሪኩ መካከል፡ የተፈጠረው አለመግባባት ነበር፡፡ እንዲህ የፖለቲካውን መዋር በጨበጡት፡ በአባ ጳውሎሥ አሽናፊነት ሊጠናቀቅ። ከቤተክርስቲያኗ ሕግና ደንብ ውጭ ታጋይ ገብረመድህን፡ ያለመምኑ ይሁንታ ፡ በተረ ሥልጣኑን፡ በፖለተካ ሹመት፡ ከተቆናጠጡበት፡ ጊዜ ጀምሮ፡ ይህች ቤተክርሥቲያን፡ የፍቅር፣ የሰላምና የአንድነት ማሥተማሪያ፣ የወንጌል መሥበኪያና የሐጢያት ማሥተሰርያ ጽሎት ማድረሻነቷ ቀርቶ የንግድ፣ የጸብ፣ የክርክርና የንተርክ መድረክ ሆናለች። ለምሣሌ የፖለቲካ ሹመኛው ሥራቸውን ሲጀምሩ፡ እነ አለቃ አያሌው ታምሩንና፡ እነ ሊቀካህናት አባይነህ አበበን፡ የመሣሰሉ ታላላቅ ሊቃውንት ያለበቂ ምክናያት፡ ከእናት ቤተክርስቲያናቸው፡ እንዳይደርሱ ሲያግዷቸው፡ የዛሪዎቹ ተረኛ ጳጳሣት፡ ለምን የሚል ጥያቄ አላቀረቡም ነበር ብቻ ሣይሆን፡ ብዙዎቹ ይበል የሚል ምልክት እየሰጡ፡ የሥልጣን ብልግናውን ሲያበረታቱ የነበሩ ናቸው። እንግዴህ ነገሩ መበላሸትና ሃይማኖታዊ ሥርአቱም ፈሩን መሣት፣ ቤተክርሥቲያኗም የፍቅር በር መሆኗ መቅረት፡ አሀዱ ያለው በዚያ ወቅት ነበር፡፡ እያደር ብጥብጡ ተስፋፍቶ መላ ሐገሬቷን ሲያዳርስም፡ በአባ ጳውሎሥ ዙሪያ ከተኮለኮሉ፡ ጳጳሣት መካከል አንዱም ስለሰላምና ፍቅር ለመናገር አልሞከሩም፡ ሥለ እውነት ግን በየትኛውም፡ የእምነት ተቋም ውሥጥ፡ ፍቅር በሌለበት ሁኔታ ላይ ሆኖ እግዚያብሔርን አገለግላለሁ፡ ማለት አስቸጋሪ ይመሥለኛል። ምክናያቱም በመጀመሬያ፡ ጌታችንና መዳህኒታችን ለሰው ልጆች ያስተማረው ባለእንጀራህን፡ እንደ እራሥህ ውደድ እንጅ ጥላ፣ አሣድድ፣ በድል በማለት አይደለም። የእግዚያብሔርን ትዕዛዝ በመፈጽም እረገድም አርያ ሆነው መታያት የነበረባቸው ደግሞ ጳጳሣት ነበሩ ብየ አስባለሁ። ውድ አንባብያን ይህንን አባባሌን የበለጠ ግልጽ ያደርግልኝ ይሆናል ብየ ሥለአሰብሁ፡ የጌታችን የመዳህኒታችን፡ የእየሱስ ክርስቶስ፡ደቀመዝሙር የሆነው ሐዋርያው ጳውሎሥ ወደቆረንጦስ ሰዎች፡ መልዕክቱ በሀዋርያት ሥራ፡ ከምዕራፍ 13 እስከ 14 ካሰፈረው መካከል ሥለፍቅር ያለውን እንደሚከተለው ልጥቀሥ((በሰዎች ወይንም በመላእክት ቋንቋ የመናገር ችሎታ ቢኖረኝ፡ እንኳን ፍቅር ከሌለኝ እንደሚጮህ ናሥና እንደሚንሿሿ ጽናጽል መሆኔ ነው። ትንቢት የመናገር ስጦታ ቢኖረኝና፡ ሚስጥርንም ሁሉ ብረዳ፡ ተራራን ከአንድ ቦታ ወደሌላ ቦታ የሚያዛውር እምነትም ሁሉ ቢኖረኝ፡ ፍቅር ከሌለኝ ከንቱ ነኝ፣ ያለኝን ሁሉ ለድሆች ባካፍል፣ ሥጋየም እንኳን ሣይቀር በእሣት እንዲቃጠል፡ አሣልፌ ብሰጥ ፍቅር ከሌለኝ ምንም አይጠቅመኝም። ፍቅር ታጋሽ ነው፣ ፍቅር ደግ ነው፣ ፍቅር አይመቀኝም፣ ፍቅር አይታበይም፣ ፍቅር አይኮራም፣ ፍቅር ሥራተቢሥ አይደለም፣ ፍቅር እውነት በሆነ ነገር ላይ ይደሰታል እንጅ፡ ውሸትና ክፋት አያሥደሥቱትም፣ ፍቅር ሁሉን ችሎ ይታገሣል፣ ፍቅር በሁሉም ላይ እምነቱን ይጥላል፣ ፍቅር ሁልጊዜ ይኖራል፣ እንጅ አይጠፋም። ትንቢት የመናገር ሥጦታም ቢሆን ጊዜያዊ ሥለሆነ ይጠፋል፣ በአዲስ ቋንቋ የመናገር ችሎታም ቢሆን ጊዜያዊ ሥለሆነ ይሻራል፣ ዕውቀትም ቢሆን ይጠፋል፣ ምክናያቱም የምናውቀውም ሆነ ትንቢት የምንናገረው፡ በከፊል ነው ነገር ግን ፍፁም የሆነው ነገር ሲመጣ ከፊል የሆነው ነገር ይሻራል። እንግዴህ እምነት፣ ተሥፋ፣ ፍቅር፡ እነዚህ ሦሥቱ ጸንተው ይኖራሉ፡ ነገር ግን ከእነዚህ መካከል ብልጫ ያለው ፍቅር ነው)) ብሏል የጥቅሱ መጨረሻ። በበኩሌ ከዚህ መልዕክት፡ የምገነዘበው፡ ፍቅር ማለት እግዚያብሔር ማለት እንደሆነና፡ ፍቅር ማጣት እግዚያብሔርን እንደማጣት ነው። እናም እግዚያብሔር የሌለበት፡ የሀይማኖት ተቋም ወይንም ቤተክርሥቲያን አይደለም፡

የግለሥብ ህይወት እንኳን ዋጋቢስ እንደሆነ ነው። ሐዋርያው ጳውሎስ የነገረን፡ ይህንን ይዘቱ ጥብቅ፡ ሚሥጥሩ እሩቅ የሆነ፣ የጠለቀና የመጠቀ መንፈሣዊ አስተምሮ፡ የዛሪዋ ኢትዮጵያ የሐይማኖት አባት ተብዬ፡ ታጋይ አባ ገብረመድህን ወይንም አባ ዲያብሎስ፡ እና ተከታዮቻቸው ወደጎን ገሸሽ በማድረግ፡ ፍቅር የሆነውን እግዚያብሔርን ክደው፡ የጥፋትና የእርኩሥ መንፈሥ መልክተኛውን መለስ ዜናዊን ፡ በመተካት በእሱ እያመለኩና እየማሉ፡ እንሆ አገልጋይና መምኑን ማመሱን፡ እምነትና ሐይማኖቱን ማፍረስ፣ ማርከሥና ማኮሰሱን ተያይዘውታል። የታጋይ ጳውሎስንና የተከታዮቻቸውን፡ በምድሩ ዓለም በአለው ህግ ፊት ወንጀል፣ በእግዚያብሔር መንግሥት ፊት ሃጢያት የሚሆነውን ጥፋታቸውን በሙሉ ለመዘርዘር ማሰብ ስንክ እሣር፡ እንደመጻፍ የሚቆጠር ከመሆኑም በላይ የዚህ ጽሁፍ አንባቢ በሙሉ የጉዳዩ ተደራሲ ስለሆነ፡ የሚያውቀውን ደግሜ በመክተብ፡ እንዳላሰለቸው፡ ልተዎውና ጠቅለል ባለመልኩ ለመግለጽ፡ ግን እድሜ ለአባ ዲያብሎሥ ዛሪ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ፡ ተዋህዶ ቤተክርሥቲያን በእምነት ፋንታ ክህደትን፣ በደግሥራ ፋንታ ክፋተን፣ በእውነት ፋንታ ውሸተን፣ እራሥን ለመንፈሣዊ ቁም ነገር በማስገዛት ፋንታ ሽፍጥና ሀጢያትን፣ በወንድማማችነት ፋንታ ባላንጣነትን፣ በፍቅር ፋንታ ጸብን ዘርታ ዕልቂትን የምታመርት፡ አውድማና የዚህ እኩይ ምግባር ደቀመዛሙርትን የምትፈለፍል ማሽን ሆናለች፡

እጅግ የሚያሣዝነው ግን፡ አያሌ ኢትዮጵያውያን በዚህ ወረርሽኝ ተበክለው ለእነ አባ ገብረ መድህን አሣፋሪ ጽዋ ተቋዳሽ መሆናቸው ነው። የእነዚህ ሰዎች አስገራሚ ነገር ቢኖር፡ ደግሞ ህዝብ ተሸንፎ፡ አንባገነን አሸንፎ፡ ያረፍድ እንደሆን እንጅ፡ መሰንበት አይደለም መዋል እንደማይችል መገመትና ነገ ከህዝብ ፍርድ ማምለጥ አለመቻላቸውን ዛሪ ለማስታዎስ አለመፈለጋቸውም ነው። ሥለሃቅ ከእኝህ የክፋትና የጥፋት ጌታ፣ የሐጢያት ባሪያ፣ የመንፈስ ቅዱስ ጠላት የእውነት ባላንጣና ከዳተኛ ከሆኑት ከአባ ጳውሎሥ ጋር እስከመቸ በውሸት ካባ ተጀቡነን፡ ከህዝብ እርቀንና ተደብቀን፡ እንኖራለን ብለው እያሰቡ ይሆን? መልሱን ለጊዜ ልተወውና፡ ሐሣቤን ለመቋጨት ዘግይተውም ቢሆን በአሁኑ ወቅት ያባ ዲያብሎሥን ሥራ፡ እየተፋለሙ ለአሉ አባቶች፡ መልዕክት ይሆን ዘንድ፡ አሁንም ሀዋርያው ጳውሎስ ወደ ኤፌሦን ሰዎች ካሥተላለፈው ምክሩ፡ ውሥጥ ከምዕራፍ 6 ቁ/ 10 ላይ ቅንጨብ አድርጌ፡ ልጥቀስ፡ (ወንድሞቸ ሆይ በጌታና በእርሱም ታላቅ ሐይል በርቱ፡ የዲያብሎሥን የተንኮል ሥራ በመቃዎም የእግዚያብሔርን የጦር መሣሪያ ልበሱ። ምክናያቱም የእኛ ውጊያ ከሰዎች ጋር ሣይሆን በዚህ የጨለማ ዘመን፡ ከሚሰሩ ገዥዎች፣ ከባለሥልጣኖችና፡ ከዓለም ሃይሎች የእርኩሣን መናፍሥት፡ ሠራዊት ጋር ነው። ሥለዚህ የእግዚያብሔርን፡ የጦር መሣሬያ በሙሉ አንሱ እንግዴህ እውነትን እንደዝናር፡ ታጥቃችሁ ጽድቅን እንደ ጥሩር ለብሣችሁ፣ በመዘጋጀት ቁሙ) ስለአ እናንተም ይሕንን ሐያል የጦር ዕቃ፡ ከተጠቀማችሁ ሁሉንም እንደምታፈርሱን እሙን ነውና፡ በርቱ እያልሁ። ከህዝብ እምነትና ፍላጎት ባሻገር፡ ላላችሁት ደግም፡ በአንድ ነገር ላይ ላሥምር፡ ሐይማኖታዊ የሞራል አቋማቸው፡ በዘረኛ የፖለቲካ እምነታቸው፡ ተበክሎ የእግዚያብሔርን መንገድ ሥተው ሰይጣናዊ ድርጊትን፡ በማከናወን ላይ ያሉትን፡ ታጋይ ጳውሎሥን (አባ ዲያብሎሥን) የታደማችሁ፡ ብጹአን አባቶች (ጳጳሣት) ያለፈው አልፏል ለወደፊቱ፡ የህሌናን ጉድፍና የመንፈሥን እድፍ፡ ጠልቆ የሚያየውና አበጥሮና አንጠርጥሮ የሚያውቀው፡ ሐያሉ ልዑል እግዚያብሔር፡ መሥሚያ ህሌና መገንዘቢያ ልቦና ሰጥቷችሁ በድፍረት ውሸትን አጋልጣችሁ፡ አሽናፊነታቸው የግድ ከማይቀረው፡ ከህዝብና ከዕውነት ጎን በመቆም ከመንፈሣዊ ክብራችሁ ሣትለዩ ለመኖር ትበቁ ዘንድ ሐገራችሁ ኢትዮጵያ እጆቿን ወደ እግዚያብሔር ብቻ ሣይሆን ወደ እናንተም በመዘርጋት እምርራ እየተማጸነቻችሁ መሆኑን ለመረዳት ያብቃችሁ፡እያልሁ የዛሬን በምትከተለዋ የግጥምሥንኝ ልሰናበት።

## በቃ ሥም ቀይሩ

መጽሐፍ ቅዱሣችን በሐዋርያት ሥራ እንደሚያስተምረው፣
ሐሣዊ መሲሁን የበር የሱስን በቃሉ አሣወረው።
አንድ ሀገረ ገዥ ሰርጊወስ የሚባል፣
መስማት ፈለገና የፈጣሪውን ቃል፣
እንዲመጣ አስጠራው የዚያኔውን ሣኦል።
ሣኦል የነበረው ጳውሎሥም በደሥታ እየፈነደቀ፣
የፈጣሬውን ቃል በግልጽ አሣወቀ።
ሐሰተኛው ጠንቋይ ደግሞ በርየሱስ፣
ሣያፍር በመቅረብ ከጳውሎስ ድረስ፣
ተቃውሞ አሰማ በእውር በድንብስ።
ጳውሎሥ የተባለው ሣኦል ግን በመንፈሥ፣
ገሰጸው በአምላክ ሥም ብሎም አይንህ ይፍሰሥ።
የጳውሎሥም ቃሉ በቅጽበት ሰመረ፣
ሐሰተኛው ጠንቋይ አይኖቹን ታወረ።
ገዥው ሰርጊወስም አመነ በወልድ፣
አይቷልና ሐቅን ሣይዘገይ ሲፈርድ።
እውነተኛው ጳውሎሥ እንደተናገረው፣
መቸ ይሆን አምላክ ፊቱን የሚያዞረው።
የትናንቱ ጳውሎሥ ነበር እውነተኛ፣
የክርስቶስ አሽከር የህዝብ መዳኛ።
ዛሪ በኢትዮጵያ ጳውሎሥ የሚሉት፣
በመሥቀሉ ፋንታ ሽጉጥ በማውጣት፣
ይግድላሉ ሰውን ያላንዳች ሐፍረት።
በሽታው ጥይቱ እራብ እርዛቱ፣
ወገንን ሲያረግፈው እንዲህ በእየለቱ፣
ትንፋሽ አያሰሙም ጳውሎስ የውሽቱ።
ኦርቶዶክሥ ሐይማኖት ከጥንት ከጥኋት፣
ትመራ ነበረ በመንፈሥ አባት፣
አውግዞ ጸልዮ በሚያወርድ ምህረት።
ዛሪ በካድሬ እንዲህ ሥትመራ፣
መፈልፈያ ሆነች ለአሣር ለመከራ።
እግዞበል ወገኔ ወደፈጣሪሕ፣
የውሽቱን ጳውሎሥ እንዲ ነቅልልሕ።
በቃ ሥም ቀይሩ ታጋዮ ጳውሎሥ፣
የሐዋርያው ሥም በእርስዎ አይርከሥ።
የሐዋርያው ስም በእርሥዎ አይርከሥ።

email:  matebemelese@yahoo.com